# ሁለት ጦርነቶች፤ ( ክፍል አንድ )

( ያልተጻፈ ታሪክን ለመዘከር )

አንዱዓለም ተፈራ

እሁድ፤ መስከረም ፯ ቀን ፳፻፲ ዓመተ ምህረት ( 9/17/2017 )

ታሪክን የሚጽፉትና የሚጻፍላቸው፤ አጥቂዎች ናቸው ይባላል። ዕውነትም ናቸው። ቀለሙን፣ ወረቀቱን፣ ብዕሩን ከነጸሐፊውና ከማሰራጨት ጉልበቱ ጋር ባለቤቶቹ እነሱ ነውና! አርበኝነት ግን የአጥቂዎቹ የግል ንብረት አይደለም። ጀግንነትም የአጥቂዎቹ የግል ንብረት አይደለም። ቆራጥነትም የአጥቂዎቹ የግል ንብረት አይደለም። ድፍረትም የአጥቂዎቹ የግል ንብረት አይደለም። ልበ ሙሉነትም የአጥቂዎቹ የግል ንብረት አይደለም። ሞት አይፈሬነትም የአጥቂዎቹ የግል ንብረት አይደለም። የጥይት ጋጋታን መጋፈጥና ከጎኑ ላለው ጓዱ ቀድሞ መጋፈጥም የአጥቂዎቹ የግል ንብረት አይደለም። አጥቂ መሆንና አለመሆን፤ ከነዚህ የግለሰብ አስተዋፅዖዎች በተጨማሪ፤ ወሳኝ የሆኑ ብዙ ሌሎች ክንውኖች አሉ። የጦር ሜዳው ተጋድሎ ሌላ ነው። የአጠቃላይ ትግሉ ስኬቱ ደግሞ ሌላ ነው። ምሳሌ ይሆኑ ዘንድ፤ የሁለት ጦርነቶችን ውሎ፤ ባጭሩ አከታትዬ አቀርላችኋለሁ። ላሁኑ መግቢያቸው ይኸውና።

ስለጦርነቶች፤ በጦር ሜዳ የዋሉ ብቻ መጻፍ ቢፈቀድላቸው፤ የተከታይ ጦርነቶች ቁጥር ከግማሽ በላይ በጣም ያንስ ነበር። እኒህ ቢጽፉትና ሲጽፉት፤ የፈሰሰው ደም ትንፋግ ይሰነፍጣቸዋል። የተሰበረው አጥንት ቆሞ ይወጋቸዋል። የጠፋው ንብረት፣ የተበተነው ቤተሰብ፣ በአእምሯቸው የተጻፈው ታሪክ፤ በምንም መንገድ ጦርነትን እንዲያሞግሱ፣ እንዲያደንቁና ወርቅ እንዲቀቡት አይፈቅድላቸውምና! ጦርነትን እንደ ጦርነት ያቀርቡታልና! ጦርነት፤ በአንዲት አጭር በክንውን የተጠቀጠቀች ወቅት፤ ወጣቶች አድገው አርጅተው ዕድሜያቸውን ጨርሰው ሕይወታቸው የሚያበቃበትና ወደ ምድር አፈር ሊሆኑ የሚገቡበት ሁኔታ ነው። ሲኒማን ለሚያዩ፤ የተዋኒያኑን ተኩስ ልውውጥ ሲያደምጡ፤ ያደንቃሉ። በጦርነት የዋሉ ግን፤ ተኩስ ሲሰሙ አብሮ የሚመጣ ሰቅዞ የሚይዝ ትዝታ፤ በደም የተጨማለቀ ቀፋፊ ሺፋን ዓይኖቻቸውን ይጋርደዋል። በጦርነት ለዋሉ፤ ጦርነት አልፏል ብለው የሚረሱት ጉዳይ አይደለም። ይልቁንም ለቀሪ ሕይወታቸው የማይጨረስ የቤት ሥራ የሠጣቸው አዛዣቸው ነው። ማንነትን ከመኖር ትርጉም ጋር፤ ደጋግሞ ይጠይቃቸዋል። ማለቂያ የለውም። ማለቂያው መቃብር ሲወርዱ፤ በላያቸው ላይ የሚጫነው አፈር ብቻ ነው። የትምህርት ቤት ጓደኞቼ፣ አብሬያቸው የኖርኩ ጓደኞቼና የትግል አጋሮቼ፤ የአሰበ ተፈሪዎቹ ሰይፉ ጠናና እዮብ ጠና፤ በያንዳንዷ ሌሊት፤ ገጽታቸው በፊቴ ሕያው ይሆንብኛል። የሰንዳፋው ወታደር እንዳለና ማይጸብሪ የቀረው ነመራ፤ ፊታቸው መንገዴን ይዘጋዋል። ጦርነት፤ በቦታው ለዋሉበት ሁሉ፣ በጎን አጥንት እንደተሰካ ጦር አብሮ የሚኖር ሀቅ ነው።

ማንኛውም ጦርነት ወጣቶችን ይማግዳል፣ የጥይት ጋጋታን ያስተናግዳል፣ እናም በሌሊቱ ድፍን ጨለማ፤ ጥይቶችን እያቀላና እያበራ ሀገሩን ያሽቆጠቁጣል። የከባድና ቀላል መሳሪያዎች እሩምታ ጆሮን ሳይጋበዙ ይዥጎደጎዱበታል። የልብን የድፍረትና የማንነት ጥያቄ ደጋግመው ትርታውን አጅበው ይጠይቁታል። ደም ይቀዳል። አጥንት ይሰበራል። ያለ የነበረ ይሆናል። ስቃይ አየሩን ይሞላል። እናትና አባት ቢጠሩ አይሰሙም። በዚያ ቦታ የሰው ሕይወት ሳይሆን፤ የነገ የኅብረተሰብ ሂደት ይወሰናል። ያ ነው ጦርነት።

እኒህ የመርጥኳቸው ሁለቱ ጦርነቶች፤ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት አባል ሆኜ፤ የተሳተፍኩባቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው የጦርነትን ምንነት የሚያሳዩ ናቸው። ይህ የግል ታሪኬ አይደለም። ይህ አብረውኝ የነበሩ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት ታጋዮች ታሪክ ነው። ድርጅቱ ለድል ስላልበቃ፤ ሐውልት ሳይቆምለት፤ ታሪኩ እንዲነበብ፤ ሳይጻፍና ለሕዝቡ የመቅረብ

ዕድል ሳያገኝ ቆይቷል። ተመራማሪዎች ለወደፊቱ ብዙ ይጽፋሉ። እኔ በሕይወት እያለሁ ይሄን ትዝታዬን ማካፈል ግዴታ አለብኝ። እዚህ ላይ የማሰፍረው፤ ያንን ግዴታዬን ለመወጣት ሳይሆን፤ አጉል በአጥቂዎቹ እነሱን በሚያንቆለጳጵስ መንገድ ተዛንፎ የተጻፈውን ለማስተካከል ነው። ከነኝህ ሌላ ብዙ የተሳተፍኩባቸው ጦርነቶች ነበሩ። በምንም መንገድ ቢሆን የከፉና የረዘሙ፣ የቆሰልኩባቸውና የቅርብ የሆኑኝን ያጣሁባቸው፤ ነበሩ። ሁሎችን በዝርዝር ልግለጥ ማለት፣ አሜሪካ ገብቶ እያንዳንዱን ከተማ ልይ ማለት ነው። የአሜሪካ ከተሞች አንዱን ካዩ ሌሎቹን በሙሉ ዓዩ ማለት ይቻላል። በሺዎችና በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ መሽከርከሪያዎችን የሚያስተናግዱ፤ ያባይን ጠመዝማዛ ሸለቆዎች የሚመስሉ መስፈንጠሪያ አውራ ጎዳናዎች፣ የደምቢያን ተራሮች የሚያስንቁ ሕንፃዎች፣ ካንድ እናት የተወለዱ የተለያዩ ልጆቿን የሚመስሉ የሰዎች መኖሪያ ቤቶች ናቸው። የዎልኩባቸውም ጦርነቶች እንዲሁ፤ ጓዶቼ የተሰውበት፣ የጥይት ጋጋታ የበዙባቸው፤ ደምና ስቃይ የተንዶቀዶቁበባቸው፣ የወጡ በሙሉ፤ ሲወጡ እንደነበሩ ሞልተው ያልተመለሱባቸው ነበሩ። ስለዚህ ስለሁለቱ ስናገር፤ ስለዋልኩባቸው ጦርነቶች በሙሉ ነው።

የመጀመሪያውን ከዚህ ከመግቢያው በማስከትለው ሁለተኛው ክፍል ሳቀርበው፤ ሁለተኛውን ደግሞ ከዚያ በሚከተለው በሶስተኛው ክፍል አቀርበዋለሁ። የመጀመሪያው ጦርነት፤ ለኔ በመጀመሪያ ጊዜ በትልቅ ጦርነት ላይ የዋልኩበት፤ አዳርቃይ ከተማ አጠገብ፤ የአባ ማር/የማይልሃም ጦርነት ነው። በዚያ ቦታ ከደርግ ሠራዊት ጋር፤ ጥቅምት ፲ ፱ ፻ ፸ ዓመተ ምህረት፤ ፊት ለፊት የተጋጠምንበት ነበር። ሁለተኛው ደግሞ ወልቃይት ሽረላ ላይ በ፲፱፻፸፫ ዓመተ ምህረት፤ ተከዜን ተሻግሮ ከመጣው የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር ሠራዊት ጋር ያደረግነው ጦርነት ነው። እንግዲህ በሶስት ክፍል ለያይቼ የማቀርበው፤ ትንሽ ትንሹን ለማንበብ ይረዳችኋል የሚል ዕምነት ይዤ ነው። የመጀመሪያውን ጨርሳችኋል፤ ሁለተኛውን አስከትዬ አቀርብላችኋለሁ።

# ሁለት ጦርነቶች፤ ( ክፍል ፪ )

*( ያልተጻፈ ታሪክን ለመዘከር - የማይልሃም ጦርነት )*

*አንዱዓለም ተፈራ*

*እሁድ፤ መስከረም ፰ ቀን ፳፻፲ ዓመተ ምህረት* ( 9/18/2017 )

ባለፈው የመጀመሪያው ክፍል፤ አንድን ጦርነትና ጠቅላላ ትግልን አስመልክቶ፤ በኔው መንገድ፤ በጦርነቱ የዋሉ ሲጽፉት ምን ሊሆን እንደሚችል ጠቁሜ ነበር። በዚያው ውስጥ፤ ስለ ሁለት ጦርነቶች ልገልጽላችሁ ቃል ገብቼ ነበር። በዚህ በሁለተኛው ክፍል፤ ከደርግ ወታደሮች ጋር አባ ማር በሚባለው ስፍራ፤ ማይልሃል ላይ ያደረግነውን ጦርነት አትትላችኋለሁ።

አንድ ጦርነት ከመሬት ተነስቶ አይደረግም። ምክንያቶች አሉት። ዝግጅቶች አሉት። ሂደት አለው። ውጤት አለው። ጥፋት አለው። የዚህ ጦርነት ተቧዳኞቹ፤ በወቅቱ የነበረው የሰው በላው መንግሥቱ ኃይለማርያም ወታደራዊ አምባገነን ደርግ መንግሥት ወታደሮች ባንድ በኩል፤ በሌላ በኩል ደግሞ፤ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የታጠቀ ክንፍ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ) ነበር። ይህን ጦርነት፤ በኢሕአሠ ተጠንቶ፣ ታቅዶና ተወስኖ የተካሄደ ነበር። ነገሩን ለማብራራት ያክል፤ የዚህ ጦርነት የጦር አዛዥ ሆኖ እንዲመራ የተመደበው፤ የመቶ አለቃ አያልሰው ደሴ ነበር። ጦርነቱ ታቅዶ ሊደረግ የነበረው፤ ከአንድ ሳምንት በፊት፤ ከአዲስ አበባ ተነስቶ ወደ አስመራ ሲጓዝ በነበረው ሠራዊት ላይ ነበር። ያን ጉዞ፤ ሁኔታውን ዓይቶ ከመረመረ በኋላ፤ የመቶ አለቃ አያልሰው ደሴ፤ የማፈግፈግ ዕዝ አስተላለፈ። የኛ ሠራዊት አባላት፤ በጣም ቋምጠን ስለነበር፤ በጣም እየተናደድንና እየተበሳጨን፤ ወታደራዊ ትዕዛዝ ሆኖብን፤ ሳንወድ በግድ አፈገፈግን።

ወዲያውኑ ሂስና ግለሂስ በሚል፤ ስሜትን እንጂ ምክንያትና ሁኔታን ባላገናዘበ የወጣት ውርጅብኝ፤ ከማናችንም በላይ ልምዱና ዕውቀቱ የነበረውን ጓዳችንን፤ በዕቅዱ ኃላፊነቱን አልተወጣም በማለት ወረድንበት። እጅግ በጣም ታጋሽና ትሁት የሆነው የዕቅዱ አዛዥ፤ የመቶ አለቃ አያልሰው ደሴ፤ ሂሱን ሁሉ ተቀብያለሁ በማለት፤ ቁጣችንን አስተናገደ። በሳምንቱ ተመሳሳይ አጋጣሚ ተፈጠረ።

ማይልሃም ከአዳርቃይ ትንሽ ወጣ ብሎ ያለ የተራራዎች ሰንሰለት ነው። ከአዳርቃይ አልፎ ቡያ፣ ከዚያ ማይጸብሪን አልፎ ወደ ተከዜ ድልድይ የሚያመራ መንገድ አለ። ከሊማሊሞ ወርዶ በድብ ባህርና ዛሬማ የሚኮለው መንገድ፤ ጎንደርን ከአስመራ ያገናኛል። ያን ቀን የተሰለፉት ከ ፳፬ የሚበልጡ መኪናዎች፤ ለዚሁ ደፈጣችን ሆን ተብሎ የተሰናዱ ይመስላሉ። ቦታው ደግሞ ለዚህ ደፈጣችን ሆን ተብሎ የተሰራ ነበር የሚመስለው። የኛ ዝግጅትና የነሱ ንዝህላልነት በተመሳሳይ መልኩ ተሰናድቷል። የደፈጣ ውጊያው አዛዥ ደግሞ፤ ገና ሲወለድ ይሄን አድርግ ተብሎ ለዚህ የተፈጠረ ነበር ያስብል ነበር።

በአንድ መቶ ሃምሳ አካባቢ ያለ ነበር ቁጥራችን። ከባድ መሳሪያ አልነበረንም። የታጠቅናቸው መሳሪያዎች፤ ከዓንዴ እስከ አፈ ድስትና ቤልጂግ፣ ከኤም ዋን እስከ ክላሽንኮቭ የተደበላለቁ ነበሩ። ከአስር ያነሱ የቢ አር፣ ግሬኖቭ ጂ፣ የእንግሊዝ መትረየስና አገልግል መትረየስ ነበሩን። የሕክምናውም ሆነ የስንቅ ቅብብል ዝግጅታችን የማያኮራ ይዘት አልነበረውም። በኛ በኩል፤ ልበ ሙሉነቱና ድፍረቱ፣ ሞት አይፈሬነቱና ጥድፊያው፤ የአዘዞ ሎዛ ማርያም አስተሮዬና ሚስቱን ለማምጣር የሚሄድ ሙሽራ ዝግጅት እንጂ፤ የጦርነት አይመስልም ነበር። እኔ ተራራዎቹ እንደ “ሪ” ፊደል ጠምዘዝ ብሎ፤ በቀጥታ ለመቶ ሃምሳ ሜትር ተጉዞ ሊታጠፍ ሲል፤ ተኩሱን ከሚጀምሩት ወገን፤ ከላይ ከተራራው ላይ ተመድቤ ነበር።

ከተራራው ወገብ ላይ፤ ከፍተኛውን ጉዳት የሚያደርሱና፤ ከጠነከረባቸው ወደ ላይ መውጣት ያለባቸው ጓዶች ተሰልፈዋል። አዳርቃይ በቆየበት ጊዜ፤ የስለላ ክፍላችን አጠቃላይ በሆነ መንገድ፤ የወታደሩን ብዛትና አሰላለፍ፤ የመኪናዎቹን ቁጥርና አካሄድ መረጃ አቀብሏል። ባለፈው ሳምንት ማፈግፈጉ ከታዘዘበት አንዱ ምክንያት፤ የወታደሮቹ አዛዥ፤ የኛን እንቅስቃሴ በመጠርጠር፤ በእግራቸው ተራራዎችን እንዲወጡና ጥንቃቄ እንዲያደርጉ፤ ቀዳሚ ቡድን ልኳል የሚል መረጃ ነበር። ይህ ግን በወቅቱ ለአመራሩ ቅርብ ስላልነበርኩ፤ የሰሚ ሰሚ የነፈሰልኝ ነበር። በአሁኑ ጉዟቸው ግን፤ ያን አላደረገም አዛገቻቸው። ልክ እንደፈልግነው ገቡልን። እንድምትገምቱት ተኩሱን ስናንዶቀድቅባቸው ፍጹም ዝግጁ አልነበሩም። በመኪናዎቻቸው ዙርያና ወደኛ ሊያወጣ በሚችለው አቀበት መጠጊያ አድርገው ሊሰባሰቡ ሞከሩ። ሳናበርድ አርከፈከፍንባቸው። በሚችሉት ተዋጉ። ችግራቸው ግን፤ በማን ላይ እንደሚተኩሱ፣ የሚተኩስባቸው የት እንዳደፈጠ፤ ማወቅ ቀርቶ መገመት አልቻሉም ነበር።

ከመካከላቸው አንድ ጠንካራ የመቶ አለቃ አይበገሬ ሚሊሽያ ነበር። እሱ ከወዲያ ማዶ ምሽግ አበጀና፤ በቅርብ ያገኛቸውን፤ “አይዟችሁ!” እያለ፤ ማጠናከር ያዘ። ዋና አዛዣቸው ሻለቃ ፈለቀ ( ጌታቸው ) እጁን ሠጠ። የሱ እጅ መሥጠት ለኛ ምን ያህል የልብ ልብ እንደሆነን መገመት ትችላላችሁ። ከሱ በተገኘው መረጃ መሠረት፤ ድጋፍ ጠይቆ እንደማያገኝ እንደተነገረውና እንደማይመጣለት ተገለጸልን። ሊያስቸግር የሚችለው ያ መቶ አለቃ ብቻ እንደሆነ አስረዳ። ወዲያው የአንዷ የኛ ኃይል መሪ ( የሻምበል አዛዥ ) ወደኛ የመቶ ሲመጣ ዓየሁት። ጓድ በርሄ ነበር። “አስር ተቀላቀል የሚገቡ እፈልጋለሁ!” ብሎ ሲናገር ሰማሁት። ከኔ በፊት ከሠራዊቱ የቆዩ ሲቁነጠነቱ ዓየሁ። ቀደም አልኩና፤ “እኔ አለሁ!” አልኩና ተሰልፍኩ። የመቶ መሪያችን በሪሁን፤ “እሺ!” አለኝ። ፀጋዬ ዳጉሳና ሌሎቹን ሆነን አስራችን ወደ ሰሜን ምሥራቅ በማምራት፤ ከተጓዡ ወታደር መኪናዎች ቅድሚያ ገሰገስን።

ስሌቱ፤ ከፊት ለፊት ቀድመን በመሄድ፤ መንገዱን ተሻግረን፤ ከመቶ አለቃው ጀርባ ድንገት ገብተን ለመቀላቀልና ለመበተን ነው። ወደ ሃምሳ የሚጠጉ እንደሆኑ ገምተናል። ሞርታር ጠምደዋል። ፉከራውን ይለቁታል። ጥይት እንደ አሸዋ ይዘዋል። እኛ እያንዳንዳችን በወገባችን የያዝናት ብዙ የተተኮሰባት ወደ ሃያ እንኳን የማትሞላ ጥይቶችን የያዘች ከረጢት ነበረችን። እኔ፤ ለኛ፤ “ከባድ!” የተባለውን ኤም ፎርቲን ይዣለሁ። በጥድፊያ መንገዱን አቋረጥንና፤ በጥሻዎቹ ተከልለን ስንገሰግስ፤ አንድ ጎጆ ደረስን። ጎጆዋን ተገን አድርገን ስንሄድ፤ ቂጡን ወደ ጎጆው የላከ ቀፎ፤ አንዳችን ነካነውና ንቡ ገነፈለ። አጠገቡ የነበረው ጓድ ባንዴ ተወረረና ፊቱ ተደፈነ። እንደምንም ብለን ይዘነው፤ በጆቻችን ንቦቹን እየለቀምን እየጣልን ወደ ኋላ ወደ ተውናት አንዲት ትንሽ ወንዝ ሄድን። እሱን ፊቱን እያጠብን ሳለን፤ የመቶ አለቃው ወደ ተከዜ ለማፈግፈግ፤ ወታደሮቹ የሚችሉትን ሁሉ ተሸክመው፤ ከቁመት በላይ የሆነውን ሳርና ጥሻውን እያተረማመሱ መጡብን። ፈጠን ብለን ወደ ጥሻው ስንገባ፤ በደመ ነፍስ የሚጋልቡት ወታደሮች፤ ሩጫቸውን ቀጠሉ። ከኋላቸው እየተኮስን ተከተልናቸው። ሩጫቸው ግን የማንንም የፍጥነት ልኬት ያስከነዳ ነበር። ብዙም አልተከተልናቸውም።

በኛ በኩል፤ ሠራዊታችን ያለ የሌለውን ሁሉ ለዚህ ጦርነት ስለማገደ፤ ተጨማሪ የምንጠራበት ወይንም ተጠባባቂውን በር ዝጋ የምንልበት ሁኔታ አልነበረም። ያካባቢው አርሶ አደር ግን፤ “የሰከረ አሳ እንዳያመልጥህ!” እያለ እየተጠራራ ተከተላቸው። ተኩሱ ተከዜ ገብተው የራሳቸውን ወገን እስኪቀላቀሉ ድረስ አላባራም ነበር። የእኛ አመራር የተማረኩትን ወታደሮች ( ፻፬፱ ነበሩ ) መሰብሰብ ነበረበት። የመኪናዎቹን ዕድል መወሰን ነበረበት። የምንችለውን ያህል ዕቃ ሰበሰብን። ለረጅም ጊዜ ያገለገለን፤ ለያንዳንዳችን የሚሆን ብዙ የመተኛ አቆማዳ አገኘን። ከመሳሪያዎቹ ሌላ፤ ምግብና የመኝታ ልብሶች

ለቀምን። የተረፈውን ለአርሶ አደሩ የሚችለውን እንዲወስድ አድርገን፤ ሌላውን ለሳት ዳረግነው። መኪናዎቹንም ጭምር። መኪናዎቹን የምንወስድበት ቦታና መንገድ አልነበረንም። ምርኮኞቹን ለሶስት ቀን አስተምረን ወደ ደርግ መለስናቸው። በዚያ የተገኘው መሳሪያና ቁሳቁስ፤ የኛን ሠራዊት ባጠቃላይ ከፍተኛ በር ከፈተለት። ወደፊትም አሳደገው።

ያን ያህል የወቀስነውን ጓድ አያልሰውን ያመሰገነው አልነበረም። በጥፋት ጊዜ አፋችንን ያሾልነው ጓዶች፤ እሱን ለማመስገን ጊዜ አልወሰድንም። እሱ ግን ከትዕግስቱ ጋር ወደፊት ቀጠለ። በሠራዊት ደረጃ፤ እጅግ ቁጥራችን ያነሰ፤ ወታደራዊ ሥልጠናችን ብቃቱ አጠያያቂ፣ ትጥቃችን አልባሌ፣ የሆን ተዋጊዎች፤ በልባችን በያዝነው የሕዝብ አገልጋይነት ፍላጎት፤ ከእጥፍ በላይ የሆነውንና የሠለጠነ፣ እስካፍንጫው የታጠቀ ጦር ማጥቃት ብቻ ሳይሆን፤ ከሞላ ጎደል ደመሰስነው ማለት በምንችልበት ሁኔታ አቸንፍነው። ይህ ነው የዚያ ውጊያ ታሪክ። በወቅቱ የሞቱትን የወታደሮች ቁጥር እኔ ረስቸዋለሁ። የኔ የመቶ አዛዥ የነበረው በሪሁን፤ ሞርታር ተተኩሶ፤ ከአለት ጋር ተጋጭቶ ተስፈንጣሪው ግንባሩ ላይ መቶት መቁሰሉን አስታውሳለሁ። ከዚይ ሌላ ግን የማስተውሰው፤ የሞተ ቀርቶ የቆሰለ የለም። ይህ የኔ ግንዛቤ ነው።

የዚያ ጦርነት ስኬት፤ ከላይ እስከታች የነበረው የሠራዊቱ ቆራጥነት፣ ድፍረት፣ ለሞት ዝግጁነት፣ በመዝሙራችን እንደተቀመጠው “የትግሉ ነው ሕይወቴ!” ማለታችን፤ “በትግል መሞት ሕይወት!” ማለታችን ነበር። ስነ ሥርዓቱና ሕጉ ከልባችን መመንጨቱ፤ ዕምነታችን ነበር። በወረቀት ስለ ሠፈረ ሳይሆን፤ ለትግሉ የወጣንበት ዓላማ ስለነበር ነው። ባካባቢው ካለው ሕዝብ ጋር አንድነታችን ነበር። ሕዝቡ ስንቅ በማቀበል ተሳትፏል። ዕቃ በማጓጓዝ ረድቷል። ውሃ አጠጥቶናል። ያ ነበር የመጀመሪያው ጦርነት።

# ሁለት ጦርነቶች፤ ( ክፍል ፫ )

*( ያልተጻፈ ታሪክን ለመዘከር - የሽረላ ጦርነት )*

አንዱዓለም ተፈራ

እሁድ፤ መስከረም ፱ ቀን ፳፻፲ ዓመተ ምህረት ( 9/19/2017 )

ባለፈው የመጀመሪያውና ሁለተኛው ክፍሎች፤ የጦርነትን ምንነትና በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት ውስጥ ሆኜ የዋልኩበትን የመጀመሪያውን ትልቅ ጦርነት በመዘከር፤ የጓዶቼን ቆራጥነትና ሞር አይፈሬነት አስመልክቶ፤ የኔን ግንዛቤ አቅርቤላችኋለሁ። በዚህ በሶስተኛውና በመጨረሻው ክፍል፤ ወልቃይት፤ ሽረላ ላይ በኢሕአሠና በትግሬዎቹ ነፃ አውጪ ግንባር መካከል የተደረገውን ጦርነት በዝርዝር አቀርብላችኋለሁ።

የዚህ ጦርነት መሠረቱ፤ የፍልስፍና እምነትና የፖለቲካ ይዘት ነው። ለዚህ ጦርነት ቅሬቱ፤ የትግሬዎቹ ነፃ አውጪ ግንባር፤ በኢሕአሠ ሠራዊት ላይ በአሲምባ ያደረገው ወረራ ነው። ለሁሉም ግልጽ ይሆንልን ዘንድ፤ ወደ ኋላ በመመለስ፤ በስድሳዎቹ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ወቅት፤ ለሁለቱ ወገኖች መነሻ የሆነውን ማውሳቱ ግድ ነው።

በስድሳዎቹ የተማሪዎች እንቅስቃሴ የተሳተፍነው ወጣቶች፤ በዕድገታችን፤ ወላጆቻችን እና ንጉሠ ነገሥቱ የነገሩንን ሁሉ ተቀብለን፣ “ሀገራችን የአፍሪቃ የዳቦ ቅርጫት ነች!” “ታሪኳ ወደር የምይገኝላት፣ ዘፈኗ ከዓለም አንደኛ፣ በሥልጣኔ ከሁሉም የምትበልጥ!” እና . . . ሌላም ሌላም ተብለን ነበር። በትምህርት ቤት ስለሌሎቹ ሀገሮች ስንማር፤ አብዛኛውን የተነገርነውን አፈረሰብን። እናም ወደ ራሳችን ከመመልከት ይልቅ፤ ወደ ውጪ ለማየት አእምሯችን ተከፈተ። ከወላጆቻችንና ከሀገሪቱ መሪዎች ይልቅ አስተማሪዎቻችን ታመኑ። አስተማሪዎቻችን ደግሞ የውጪ ሀገር ሰዎች ነበሩ። የራሳቸው አጀንዳ እንዳላቸው ደግሞ የወጣት ጭንቅላቶቻችን አላሰቡም ነበር።

በዚህ አጣብቂኝ፤ “ከሀገር ውስጥ የሚመነጭ ምንም ጥሩ ነገር የለም!” ብለን አእምሯችንን ቀርቅረን ዘጋን። የወቅቱ ገዥዎች ለለውጥ እንቅፋትነት ተጨብሮበት፤ በዚያን ጊዜ በዓለም እየተካሄደ የነበረው የነፃነት ትግሉ፤ በተለይም የፀረ-ቅኝ ግዛት እንቅስቃሴው ሂደት፤ ለጥድፊያ ለውጥ የነበረንን ሩጫ፤ ግለቱን አሳደገው። በሩን ለማርክሲዝም በው አድርጎ ከፈተለት። ሁላችንም ማርክሲስቶች ሆንን። ችግሩ ግን አንድ ዓይነት ሳይሆን፤ የየራሳችን ማርክሲስቶች ሆንን። የብሔር ነፃ አውጪ ነን ያሉትም ማርክሲስቶች ሆኑ። የመደብ ትግል ባዮችም ማርክሲስቶች ሆንን። ሀገር ወዳዶችም ማርክሲስቶች ሆኑ። ምን አለፋችሁ የሥልጣን ቋጫሚው፤ ሰው በላ አረመኔ መንግሥቱ ኃይለማርያምም፤ ማርክሲስት ሆነ።

የመንግሥቱ ኃይለማርያም ማርክሲዝም፤ እሱ መሪ እንዳይሆን የሚቃወሙትን በሙሉ ማጥፋትና እሱ ፈጣሪና ተመላኪ መሆን ነበር። የኪም ኢል ጁንግ ዓይነት ማለት ነው። የትግሬዎቹ ነፃ አውጪ ግንባር ማርክሲስቶች ደግሞ፤ ዐማራውን አጥፍቶ፤ በቦታው የትግሬዎችን የበላይነት የሚያመጣ የትግሬዎች ሪፐብሊክ መንግሥት ማቋቋም ነበር። የኢሕአፓ ማርክሲስትነት ደግሞ፤ የላባደሩን የበላይነት ያነገሠ መንግሥት ማቋቋምና ፀረ-ኢሕአፓ የሆኑትን ማጥፋት ሆነ። እንዲህ እየተባለ፤ የየራሳችን ማርክሲስቶች ሆነን፤ ባንድ ወገን፤ “ካንተ እኔ የበለጥኩ ማርክሲስት ነኝ!” በሌላ ወገን ደግሞ፤ “አንተ ማርክሲስት አይደለህም! መጥፋት አለብህ!” የሚል የመጠፋፊያ ምሽጎችን በማበጀት፤ ትርጉም የለሽ የርስ በርስ መተላለቁ ነገሠ። ሥልጣን የፈለገው ኃይሌ ፊዳም፤ ማርክሲዝም ብሎ አሕአፓን ማጥፋት ዒላማው ሆነ።

ሀገርና ሕዝብ የሚሉትን ማዕከል ያላደረገ፤ ሲከፋ የግለሰቦችን እብሪት የተከተለ፤ አለበለዚያ ደግሞ፤ “እኔ ትክክል ነኝ፤ ሌሎቹ ሁሉ ስህተተኞች ናቸው!” የሚል ቀኖናን ያዘለ ሂደት፤ የነገሠበት ወቅት ነበር። ያኔ

ባንድ በኩል የተማሪዎችን እንቅስቃሴ አሳቦ፤ አንድም ለኤርትራ ነፃ አውጪ ታጋዮች ከለላ ለመሥጠት፤ በሌላ በኩል ግን፤ ከሃዲ ወላጆቻቸው ያስተማሯቸውን የፀረ-ኢትዮጵያ አፍቃሪ ጣሊያን ትምህርት በመውሰድ፤ ከዘመናት በፊት የነበረን የዘመነ መሳፍንት ፖለቲካን ያቀፈ በዚሁ ቡድን አእምሮ የተጋገረ የትግሬዎች የበታችነት ስሜትን ታኮ፤ የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር ዘመተ። ኢሕአሠ በአጋሜ አውራጃ፤ አብዛኛዎቹ የድርጅቱ መሪዎች በተወለዱበት አካባቢ ሲንቀሳቀስና የአውራጃውን ሕዝብ ወደሱ ሲስብ፤ በአድዋና በሺሬ ሲንቀሳቀስ የነበረው ይህ የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር፤ ያለ የሌለውን ኃይል አግበስብሶ፤ ባልተዘጋጀው የኢሕአሠ ጦር ላይ ዘመተበት። ምን ጊዜም ቢሆን፤ ጦርነት ሲደረግ ድሉ የሚያደላው፤ ሙሉ ዝግጅት ላደረገው ነውና፤ ኢሕአሠ ከቦታው እንዲለቅ ተገደደ። ሸዓቢያ የተጫወተችው ሚና ምን ጊዜም የሚታሰብ ነው። የትግሬዎቹን ቡድን ረዳች። ሆኖም ኢሕአሠ በጀብሃ ተረድቶ ለመሰንበት ቻለ። ጉዳቱ ቀላል አልነበረም። ብዙዎቹ ተስፋ ቆርጠው ከድርጅቱ ተለዩ።

የተዳከመው ጦር ወደ ጠለምት በመምጣት አገገመ። እኔ ቀደም ብዬ፤ ሥልጠናዬን አሲምባ ካጠናቀቅሁ በኋላ፤ "ዘመዶቼ ባሉበትና ቋንቋውን የበለጠ በማውቀው ጎንደር ብሄድ፤ ድርጅቱን የበለጠ ላገለግል እችላለሁ!" ብዬ ባመለከትኩት መሠረት፤ ከአንድ ኃይል ጋር፤ ከአሲምባ በመነሳት፤ ከራያና ዘቦ በስተቀር፤ ሁሉንም የትግራይ አውራጃዎች በመሰንጠቅ፤ አጋሜን፣ ሁለት ዓውላሎን፣ እንደርታን፣ አድዋን፣ አክሱምን፣ ሽሬንና፣ ተምቤንን በሌትና ቀን በመጓዝ፤ የተከዜ ወንዝ በሞላበት በክረምት በማቋረጥ፤ ጠለምት ገብቻለሁ። ከዚያ ትንሽ ቀደም ብሎ አንድ ኃይል፤ ኃይል አስራ ሰባት መጥታ ነበር። ከኛ በኋላም ሁለት ኃይሎች በወሎ ዞረው፤ ኃይል አስርና ኃይል ሃያ ስድስት፤ መጥተው ነበር።

መለስ ልበልና የሠራዊታችንን አወቃቀር ብገልጸው እኔም ለመጻፍ፤ እናንተም ለመከተል ይረዳችኋል። ዝቅተኛው የሠራዊቱ ክፍል፤ በኤርትራ ነፃ አውጪ ግንባሮች በተላለፈልን መሠረት፤ እነሱም ከአረቦቹ በወረሱት መሠረት፤ ጋንታ ይባላል። በቀጥታ በድሮው ተወልጃ ባደግሁበት ወታደራዊ አወቃቀር ሂሳብ፤ የመቶ የሚባለውን ይመስላል። ነገር ግን፤ የአባላቱ ቁጥር፤ ከአስራ ሁለት እስከ ሃያ ያለ ነው። የቁጥሩ እንዲህ መራራቅ ጉዳዩ ወዲህ ነው። ይህ ክፍል፤ የሚያድገው፤ አዳዲስ አባላት ከከተማ፤ ካካባቢው አርሶ አደር ወጣቶች ደግሞ ሠልጥነው ሲቀላቀሉት ነው። ይህ ደግሞ በዚያ ወቅት፤ ታቅዶና ታስቦበት የሚካሄድ ሳይሆን፤ እንደተገኘው የሚደረግ ነበር። የክፍሉ ቁጥር ደግሞ፤ በጦርነት ምክንያት፣ ጓዶች ሲታመሙና ባንድ ወይንም በሌላ ምክንያት ይቀያየራል። አንዳንድ ጊዜ፤ አንዱ ክፍል በቁጥር ማነስ ምክንያት ስትታጠፍ፤ አባላት በሌሎች ክፍሎች ይበተኑና የሌሎችን ክፍሎች ቁጥር ያሳድጋሉ።

ሶስቱ ጋንታዎች ( የመቶዎች ) አንድ ኃይል ይመሰርታሉ። ይህ አንድ የሻምበል መሆኑ ነው። እኔ ጠለምት በተንቀሳቀስኩበት ጊዜ፤ ከሶስት ኃይሎች በላይ ስላላደግን፤ ከዚያ በላይ መዋቅሩ አልታሰበም ነበር። ያ ማለት፤ ሲለጠጥ አንድ መቶ ሰማንያ፤ ሲኮራመት ደግሞ አንድ መቶ ስምንት ነበርን ማለት ነው። ሲገኝ አንድ አንድ የሕክምና ጓድ፤ ለያንዳንዱ የመቶ ተሰይሟል። ሳይገኝ ደግሞ፤ ለአንድ ሻምበል አንድ ጓድ ተመድቧል። የሕክምና ጓዶች፤ በጎንደር የሕክምና ዩኒቨርሲቲ የአራተኛ ዓመት ተማሪ የሆነ ወይንም በዚያው ቁስል ለመጥረግ የሁለት ቀን ትምህርት የተሠጠው/ጣት ነበሩ። ሲገኝ የሬዲዮ መገናኛ ለአንድ የሻምበል ቡድን ተሠጥቷል። ሳይገኝ በአካባቢው ካሉት ጋር ሊያገናኘው የሚችል፤ በጅ የሚያዝ የቅርብ መገናኛ ስልክ በሻምበል አዛዡ እጅ ነበር። አልፎ አልፎ ተጠጋግነው ከውጪ የቢ. ቢ. ሲ.ን ዜና ማዳመጫ ሰባራ ሬዲዮኖች ነበሩ። የቆሰሉና የታመሙት፤ ራቅ ብሎ የድብቅ የሕክምና ቦታ በማበጀት፤ በዚያ እንዲቆዩ ይደረጋል።

ከሠራዊቱ ውጪ፤ የክፍለ ሕዝብ መዋቅር ነበር። ይህ ክፍል፤ በሕዝቡ መካከል የአስተዳደርና የትምህርት ሥራን አካሂዷል። ከቀጠና አንዱ ጠለምት ቀጥሎ የመስፋፋት ሂደቱ የተደረገው ወደ በለሳ ነበር። የበለሳው ቀጠና ሁለት ነበር። ከዚያ ወደ ቀጠና ሶስት፤ ጭልጋና አርማጩሆ ተኬደ። አራተኛው ቀጠና፤ የወልቃይቱ ክፍል ነበር። በዚህ ክፍል ተመድቤ ነበር ወደ ወልቃይት የሄድኩ። በዚህ ቦታ ለስሙ ሶስት፤ በትክክል ግን ሁለት ኃይሎች ነበርን ( የሻምበል )። በለሳ ላይ የደርግ ሠራዊት ወረራ ስላቀደ፤ ያን ለመርዳት፤ የኛዎቹ "ሁለቱ" የሻምበሎች፤ ለርዳታ ተጓዙ። የቀረችው አንድ ኃይል ተከፋፍላ፤ ከቀብትያ እስከ ጠለሎ፤ ከአውራ እስከ መዘጋና ብርኩታ ድረስ መቆጣጠር ያዝን። ተጨማሪ ተልዕኮ ደግሞ ነበረን። የኛ ኃይሎች ሲመለሱ፤ በከርን እንድናጠቃ፤ እኛ አሁን ጥናት ማድረግ ነበረብን።

እኔ አባል የሆንኩባት አንድ የመቶ ( አስራ አምስት ጓዶችን የያዘች ) ወደ ቀብትያ ሂደን። ከዚያ አራት ጓዶችን ወደ ቆላው ወደ በከር አካባቢ ሄደው፤ ከእረኞች ጋር ሆነው የበከርን ዙሪያ እንዲሰልሉ ተላኩ። የቀረነው አዲ ሕርዲን ወደ ኋላችን ትተን፤ ወደ ቁልቁለቱ ጫፍ በማቅናት፤ እንንቀሳቀስ ነበር። በዚያ ላይ ሳለን፤ ሁኔታዉን በሙሉ በሰላዮቿ አማካኝነት ስትከታተለው የነበረችው የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር፤ አዲ ረመጥን በሁለት ባታሊዮች ( ብርጌድ ) ተቆጣጠረች። ሳናውቀው አዲ ሕርዲንም ወስዳለች። አርሶ አደሮች አነቁንና፤ አዲ ሕርዲን ሳንረግጥ፤ በሾኔ አድርገን ወደ መዘጋ ወረድን።

የመጀመሪያው ግጭት የተደረገው፤ አንዲት አነስተኛ ቁጥር ያላት፤ ( ሰባት ወይም ስምንት ) የኛ ክፍል፤ ከጠለሎ ወደ አዲ ረመጥ በመጓዝ ላይ ሳለች፤ በስልፍ የሚመጣ የሰው ጋጋታ ባየችና ቆም ብላ፤ ምሽግ ይዛ ራሷን ለመከላከል ስትጠብቅ ነበር። ለካስ አዲ ረመጥን የያዘው የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር ጦር፤ መላ ወልቃይትን ለመቆጣጠር፤ አሰሳ ይዟል። ጓዶቻችን ጦር በድንገት ከፈቱበትና፤ የጠላት ጦር ሲደናበር፤ ወደ ሽረላ ከፍታዎች ተንጠላጠሉ። የድንገቱን ተኩስ ያልጠበቁ የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር አባላት፤ ባሉበት ዙሪያቸውን ሲቆጣጠሩ አደሩ። ያኔውኑ ማታ፤ ከበለሳ ይሄን ሰምቶ የገሰገሰው የኛ ሁለት ኃይልና ደጋፊ አንድ ተጨማሪ የጠለምት ኃይል ይዞ፤ እኔ ካለሁበት ጋንታ ጋር መዘጋ ተገናኘን። ገስግሰን የሽረላን አቀበት ተያያዝነው። በጨለማው ወጣን። ከዚያች ተኩስ ከጀመረችው ቡድናችን ጋር ተገናኝተን፤ ዝርዝር መረጃውን ለመሪዎቻችን ሠጠን።

አሁን ወደ ተነሳሁበት የዕለቱ ጦርነት ላምራችሁ። እኛ ወደ አንድ መቶ ሃምሳ የምንጠጋ አባላት ያሉት የኢሕአሠ አባላት ነን። የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር፤ ሁለት ሺህ የያዘ ጦር ሲኖራቸው፤ አንድ ባጣሊዮን ሊጨመራቸው በመንገድ ላይ ነበር። ተጨማሪውን ባታሊዮን ያኔ አላወቅንም ነበር። የሁለት ሺህ አባላቱን መኖር ግን አውቀናል። እነሱ ሊይዙት የሚችሉት ከፍተኛ የተራራዎችን ሰንሰለት ነበር። ያን መቆጣጠር አልቻልም። ዘግይተናል። ስለዚህ፤ አማራጫችን በስተምሥራቅ ያለውን፤ ጀርባው ወደ መዘጋ የሚወስድ ቁልቁለት ያለበትን መያዝ ነበር። ያንን አደረግን። በኛም ሆነ በነሱ በኩል፤ በየነበርንበት ከበብ የነበረው ሰፊ ዝርግ ቦታ ስለሆነ፤ ከዳር እስከዳር መሸፈኑ የግድ ነበር። እነሱ የሰው ቁጥርም ሆነ የመሳሪያ ብዛት ነበራቸው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፤ የጦርነት ግጥሚያ ስልታቸው፤ እንደ ደርግ ወታደር፤ በተኩስ ኃይልና ታጋዮቹን በመማገድ ነበር ማጥቃትን የያዙት። እኛ ደግሞ የዚያ ቅንጦቱ አልነበረንም።

በኛ በኩል ሶስቱ የመጡት ኃይሎች፤ በሰሜን፣ ደቡብና መካከሉ ላይ ተመደብ። እኛ ቦታውን የምናውቀውና በቦታው የቆየነው ጓዶች፤ የፊት ለፊት መቀላቀሉን ኃላፊነት ወሰድን። መሐል ለመሐል እኔ ያለሁበት የመቶ ተመደበ። ስለዚህ፤ ከዋናው ክፍል ለቀቅ ብለን ወደ ፊት በመጓዝ፤ መካከለኛ ከፍታ ያለውን ቦታ ሸፈን። ገና ቦታውን ከመያዛችን፤ ፊት ለፊታችን የሰው ብዛት ያለበት፤ የጉንዳን ግስገሳን የያዘ፤ ከአንድ መስመር ይልቅ፤ ሶስትና አራት ባንድ ላይ በመሆን፤ እጆቻቸውን ከፊታቸው ካለው አባላቸው ላይ

በመጣል፤ የተግመለመሉ የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር አባላት ታዩን። ለበላይ አካልና ከኋላችን ሽፋን ለሚሠጡን መልዕክት ለመሥጠን ጊዜ ሳይኖረን፤ ቀረቡን። እኔና ሌሎች ሶስት ሆነን፤ ከኛ ትንሽ ዝቅ ብላ ባካለችው ጉብታ ወረድናን፤ በመቋመጥ፤ ጠመንጃዎቻችንን አዘጋጀን። ከኋላችን የቀሩት ስድስት ጓዶቻችን፤ “ለምን እኛ ወደ ኋላ ቀረን!” በማለት ሲነሱ፤ ለኛ ሽፋን መሥጠት ግዴታቸው እንደሆነና ባሉበት እንዲቆዩ ጥብቅ ትዕዛዝ ተሠጣቸው።

አቀበቱን ለመውጣት፤ ጠመንጃዎቻቸውን በጀቻቸው አንጠልጥለው፤ አንዳንዴም በጆቻቸውን አቀበቱን እየተደገፉ የሚገሰግሱት ወጣቶች፤ ከኋላቸው፤ “እንታይ አዲሃ! ንቅድሚት!” የሚል ትዕዛዝ፤ ከነሱ አልፎ እኛ እስከንሰማው ድረስ ይቧርቅባቸዋል። ሃያ አምስት ሜትር ርቀት ላይ ሲገቡልን፤ ካለንበት በመነሳት አርከፈከፍንባቸው። የምንሰማው፤ “አደዬ! አደዬ!” ብቻ ነበር። ጠመንጃቸውን አነጣጥረው ወደኛ ለመተኮስ ዕድል አላገኙም። እኛ በላያቸው ላይ ነው የነበርነው። ወደኃላቸው በመፈርጠጥ ሲንጋጉ፤ “አታ ወዲዛ ሽራሙጥ! ንቅድሚት!” የሚል ትዕዛዝ ተሸጎደጎደባቸው። ወደፊት ሊመጡ የማይችሉበት ሁኔታ ነበር። እሱኑ ገፍትረው ወደኋላቸው ነጎዱ። ያን ትዕዛዝ ሲይስተላልፍ የነበረውን ዓየሁት። በርከክ አልኩና ተኮስኩበት። በፍጥነት ከወደቀበት ተነስቶ፤ የሚሮጡትን በሙብለጥ፤ እግሬ አውጭኙን ከነሱ በባሰ ፍጥነት ተያያዘው።

አራታችን ምንም ትዕዛዝ ሳይኖረን፤ ራሳችንም ሳንነጋገር፤ የሚፈረጥቱትን የትግሬ ተጋዳዮች እየተኮስን ተከተልናቸው። እኛም በደመ ነፍስ ውስጥ ነበርን። አሁን ግስገሳው ወደ ሽምጥ ሩጫ ተቀይሯል። እንኳንስ እነሱ፤ እኛም ጠመንጃችንን ጨብጠን መሮጥ ያዝን። ወዲያው በሁለቱ ተራራዎች መካከል ከሚገኘው ገላጣ የገበያ ቦታ ደረስን። ሁለቱ ጓዶቻችን ወደ ኋላ ቀሩ። እኔና የጋንታዋ ምክትል መሪ፤ ጓድ ገለታ፤ በዓይኖቻችን እንቀጥል የሚል ግንዛቤ ተለዋወጥንና፤ በሩቁ ያየን የነበረውን ሶስተኛውን ጓዳችንን ትተን፤ ገፋን።

አሁን ሩጫችን፤ እነሱ ደፋታውን ሲሮጡ፤ በጎኑ ያለውን ከፍተኛ ቦታ ለመቆጣጠርና በላያቸው ሆነን በነሱ ላይ ለማርከፍከፍ ነበር። በትልቁ የተራራ ሰንሰለት ላይ ያሉት መትረየሶቻቸው የሚተኩስት፤ በግሮቻችን ላይ ማረፍ ጀምረዋል። ከኛ በኩል ሽፋን ሊሠጡን ከሚችሉበት ርቀት አልፈናል። ስለዚህ ሽፋን ለኛ አይታሰብም። ሁለታችን ግን፤ የታሰበን፤ እኒህ እየተንጠባጠቡ የሚሮጡትን መደምሰስ ነበር። ገበያውን በግልቢያ ሽምጥጠን። አቀበቱን ስንያያዘው፤ ከሩቅ ያለው ተኩስ ወደኛ መምጣቱን አቆመ። እኛ አሁንም ቀጠልን። ወደ አፋፉ ስንጠጋ፤ በሁለት ቁጥቋጦዎች ውስጥ፤ ሁለት የእንግሊዝ መትረየሶች አፋቸውን አሞልሙሎለው ታዩኝ። ተኩስ ሲከፍቱ፤ ገለታ፤ “ዋይ!” ብሎ ጠመንጃውን ወደ ሰማይ ወረወረው። ምን እንደሆነ ላረጋግጥ ወደሱ ስመለከት፤ ደም የሚዦቀዦቅበትን ቀኝ እጁን በግራ እጁ ይዞ፤ በጣረሞት ድምጽ ወደ ኋላ ሮጠ። ልክ ዓይኖቼን ከሱ ሳልመልስ፤ ከመትረየሱ የተተኮሱ ሁለት ጥይቶች፤ በጀርባያ የትከሻ ማቀፊያ አጥንቶቼ ገብተው፤ የትከሻየን መጋጠሚያ ድቡልቡል አጥንት ሰብረው፤ ቅልጥሜን በመበታተን፤ ከፊቴ ደሜን ሲረጩት፤ እጄ ዝሎ የኔም ጠመንጃ ከጄ ሲወድቅ ዓየሁ።

ያን ጊዜ፤ ተኩሳቸውን አቁመው፤ “እድህ ሃባ! እድህ ሃባ!” እያሉ ከተሸጎጡበት ወደኔ ሊመጡ ሲነሱ ዓየሁ። በቀጥታ በዝግታ የኔን ጠመንጃ አነሳሁ። የገለታንም ጠመንጃ አነሳሁና፤ ሁለቱንም በግራ እጄ በግራ ትከሻዬ ላይ ሰቀልኩና፤ ቀኝ እጄን ደግፌ የወጣሁትን ቁልቁለት መውረድ ያዝኩ። አሁን ተኩሳቸውን በኔ ላይ አቁመዋል። እጄን እንደሚይዙ ተማምነዋል። ፈራ ተባ እያሉ ስለሚመጡ፤ ቶሎ ሊደርሱብኝ አልቻሉም። የኔ ጉዞ የኤሊ ጉዞ ነበር። እምነቴ ከሚይዙኝ ይግደሉኝ ነበር። ለሞት እንጂ ለመያዝ ዝግጁ አልነበርኩም።

ከቀኝ ትከሻዬ ሥር የሚጎርፈው ደም ያስደነግጣል። ነገር ግን፤ በዚያ ወቅት ማን ደምን ከቁጥር ያስገባል። ማን መቁሰልን ያቋጥራል። በደመ ነፍስ መንገዴን ቀጠልኩ።

ገለታ የት እንደገባ አላወቅሁም። ሜዳውን ተያያዝኩት። አሁን ተኩሱ ወደኔ ዞረ። እንደሽሮ ፍላት ዙሪያዬን ይንቶከቶካል። አፈሩን ከጎንና ከፊቴ ይጭረዋል። መዘመር አማረኝ። ነገር ግን ምንም የምቆጣጠረው የሰውነቴ ክፍል አልነበረም። እግሮቼም እንዲያው የተፈጥሮ ሆኖባቸው ነው፤ አንዱ አንዱን የሚከተሉት። መንገዴም በውስጥ አእምሮዬ የተቀረጸ የመጣሁበትን መንገድ ትዝታ ይዞ ነበር የተጓዘው። ልክ ሜዳውን ጨርሼ የአጋም ተክሎች ውስጥ ስገባ፤ ድካሙ፤ ውሃ ጥማቱና ቁስሉ ባንድ ላይ ተረባርበው፤ “አለቀልህ!” አሉኝ። “እንግዲያውስ ድብቅ ቦታ ፈልጌ የምሞትበትን መርጬ፤ በርግጥ እንዳያገኙኝ ሆኜ መሞት አለብኝ!” ብዬ፤ ጥቅጥቅ ወደ ሆነው ቁጥቋጦ ሄጄ፤ ተፋሰስ አገኘሁና፤ ጠመንጃዎቹን በሥር ደብቄ፥ እጄን አጣጥፌ ደረቴ ላይ በማስፈር፤ ለመጨረሻ ጊዜ ያልኩትን ዓይኖቼን ገጠምኳቸው። ሞቴን ጠበቅሁ። የተመታውን እጄን አጥፌ በደረቴ ላይ ሳስቀምጥ፤ ደም መፍሰሱን አቁሟል። አእምሮዬ ተመለሰ። ማሰብ ጀመርኩ። “እንዴ! ታዲያ ጊዜ ካለኝ፤ ለምን ወደ ጓዶች እየሄድኩ አልሞትም!” የሚል ሃሳብ መጣልኝና፤ መንገድ ጀመርኩ። ለካስ ጓዶች የኔን መጥፋት ተገንዝበውና ገለታው ደርሶ ሁኔታውን ነግሯቸው ኖሮ፤ እኔን ፍላጋ አንዲት ቡድን ተልካለች። እኔ እንቅልፍ ሽልብ አድርጎኝ፤ ፈልገው አጥተውኝ፤ ተመልሰው በመሄድ፤ “አላገኘነውም!” የሚል ሪፖርት አድርገዋል።

ውለም ዘለም እያልኩ፤ ሁለቱን ጠመንጃዎች፤ “ለጠላት አልሠጥም!” ብዬ አሁንም አንግቤ ስንገታገት፤ ጦሩን የሚመሩት ጓድ ሀድሽና ጓድ ጀማል፤ ከሰሜን ወደ ደቡብ ሲሄዱ፤ እኔን ዓዩኝ። ተሯሩጠው ወድኔ ሲመጡ፤ ተዝለፍልፌ ወደቅሁ። አጋሙን ዘንጥለው፤ በራሴው ኩሽክ ( ብጣሽ የሌሊት መሸፈኛ አንሶላ ጨርቅ ) ተነሳነስ አበጁና፤ ይዘውኝ ወደ ቁስለኞች ወሰዱኝ። እዚያ አስራ ሰባት ቁስለኞች ነበሩ። እንዳጋጣሚ የመጨረሻዋን ቲታነስ ወጉኝና፤ እዚያው በተገኘ የእንጨት ስባሪና በኔዋ ኩሽክ፤ ክንዴን ጠርዘው፤ ወደ ቆላው እንድንወርድ ትዕዛዝ ተሠጠ። በዚያ ቦታ ሳቁ ብዙ ነበር። “እኔ ላውራ!” “እኔ ላውራ!” እሽቅድድም ነበር። ከግሮቻችን ሥር ያዝረፈረፍናቸውን የጠላታችንን ሬሳ መቁጠሩ ጥድፊያ ነበር። ገለታ፤ በጁና በጠመንጃው መካከል ጥይት ያለፈችበትን ቁስሉን አሳየኝ። ከኛ በኩል አንድ ጓድ እንደተሰዋብን ተነገረን። የማዝነው፤ የዚያን ጓድ ስም መርሳቴ ነው። አርሶ አደሮች በትግሬዎቹ በኩል፤ ቅበሩ ተብለው ታዘው፤ ከሰማንያ በላይ እንደቀበሩ አጫውተውናል።

ቁልቁለቱን፤ ሙሉ ምሽቱንና ሌሊቱን ፈጅተን ወረድንና፤ መንደር ልንገባ ስንባዝን፤ “ድም! ድም!” የሚል ድምጽ ከፊታችን ሰማን። ሳሩ ከቁመት በላይና ሩቅ የማያሳይ ነበር። ግማሾቻችን በበቅሎዎች፤ ጥቂቶቹ በተነሳነስ፤ ሌሎቹ ደግሞ ተጠጋግነው በግራቸው ነበሩ። መንገዱን ለቀን አድፍጠን ማዳመጥ ያዝን። ተከዜን ተሻግሮ የመጣ ተጨማሪ ጦራቸው ነበር። በቅሎቻችንን አፋቸውን በጆቻችን ለጎምን። የማያልቅ ሰልፍ ነጎደ። የራሳችንንም ትንፋሽ በቀስታ መልቀቁ ግድ ነበር። ደቂቃው ወደ ሰዓት፤ ሰዓቱ ወደማያልቅ ቀን ሆኖ፤ አልገፋ አለ። የተደበቅነው በሙሉ ቁስለኛና የቁስለኛ ተሸካሚና ረዳት እንጂ፤ ሐኪም እንኳን አብሮን የለም። ምንም ዓይነት ትጥቅ አልያዝንም። ያሉን ሐኪሞቹም ሆነ መሳሪያ፤ በሙሉ ከሠራዊቱ ጋር ትተናቸው መጥተናል። ቢያንስ ከሁለት ሰዓት የማያልቅ ጉዞ በኋላ፤ ረገብ ሲል ተሰማን። እየተንጠባጠበ የሚቀጥልና የኋላ ተጠባባቂዎቻቸው የማይልቅ ነጠብጣብ ጠበቅን። ያማያልፍ የለምና፤ ያም አለፈ። ምሽቱን ወደ መንደር እኛን በሽክም ለመርዳት የመጡትን አርሶ አደሮች በመላክ፤ የሚቀመስ ምግብ አገኘን። ከሰባት ቀን በኋላ ሐኪሞቻችንን አገኘን። ስለቁስሎቻችን ሁኔታ መናገሩ ሌላ አዲስ መፅሀፍ ነውና፤ አላነሳውም።

ማጠቃለያው፤ እኛ በጣም አነስተኛ የሆን ጓዶች፤ ምንም የበዛ ጦር ቢያጋጥመን፤ በልባችን የነበረውን የሕዝብና ያገር ፍቅር አዝለን፤ በራሳቸው ላይ ሊደርስ ቀርቶ፤ ሲያዳምጡትም ሰውነትን እየዘገነነ፤ የሚረብሽ ሁኔታን ማለፋችንን ያሳያል። ሆኖም፤ ይህ የመጨረሻ አጥቂዎች ታሪክ ስላልሆነ፤ አለመጻፉ ብቻ ሳይሆን፤ ቢጻፍም የሚያምነው ጥቂት እንደሚሆን አልጠራጠርም። አሁንም አጥቂዎች ናቸውና ጸሐፊዎች!